





# የስነምግባር ደንብ

ይሳተፉ

መቃወም(መዋጋት) ያሉበን ነገሮች

ማክበር ያሉበን ነገሮች

ማሳውቅ

# የስነምግባር ደንብ

CASTEL
AFRIQUE

CASTEL
FAMILIAL & INTERNATIONAL

somdia
Grandir ensemble

# የዳይሬክተሩ መልእክት

በመስራቹ ፒየር ካስቴል ምኞት ከ 70 ዓመታት በፊት  የተወለደው ካስቴል ግሩፕ በጠንካራ ወጎች እና የስነ ምግባር እሴቶች ላይ የተገነባ ሲሆን  በአለም ዙሪያ እና በአካባቢያዊ ልማት ላይ እንቅስቃሴውን ማስፋፋት ችሏል እንዲሁም ለተጠቃሚዎቹ ምንጊዜም የተሻለ ጥራት ያለው ምርት ለማቅረብ ይጥራል፡፡

በአሁን ጊዜ በበርካታ ሀገሮች በወይን ጠጅ፣ በቢራ፣ ለስላሳ መጠጦች፣ በውሃ እና በግብርና ምርቶች እየሰራ ያለው ቡድን፤ የእንቅስቃሴውን ዘላቂነት ለማረጋገጥ ባለው ፍላጎት ዙሪያ ሰራተኞቹን ያስተባብራል፡፡



ሰራተኞች የድርሻቸውን ፣ ተጽዕኖአቸውን እና ኃላፊነታቸውን በመገንዘብ ለዚህ ቀጣይነት መሰረት በመጣል ፣ ታማኝነት የስኬት ቁልፍ መሆኑን በማመን የወደፊት ዕጣቸውን በጋራ ይገነባሉ

የስነ ምግባር ደንቡ ቡድኑና እና ሰራተኞቹ የእነርሱንም ሆነ የስራ አጋሮቻቸውን እድገት ለዘለቄታው ለማስቀጠል የሚረዳቸውን መሰረታዊ ስራአቶች ያካትታል፡፡

**ግሬጎሪ ክለርሲ**

ዋና ሥራ አስኪያጅ

# የስነምግባር ደንብ

# መግቢያ

የዚህ የስነምግባር ህግ አላማ **ለድርጅቱ ዲኤፍ ሆልዲንግ ኤስኤ እና ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቶቹ ሰራተኞች** እና ቡድኑ በሚሰራባቸው አገሮች በሙሉ ሰራተኞች ዕለት ከዕለት በሙያዊ እንቅስቃሴያቸው ስር ሊከተሉት የሚገባቸውን የሥነ-ምግባር ደንቦች ማስተላለፍ ነው ::

ደንቡ **መከበር ያለባቸውን ህጎች** የሚዘረዝር ሲሆን የቡድን ሰራተኞች ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ አንዳንድ ሁኔታዎችን የሚያሳይ ቢሆንም ነገርግን ሁሉንም ሊሸፍን አይችልም።

**የሁኔታዎች ግምገማ እና** የእያንዳንዱ ሰራተኛ ወሳኔ ሲሰጥ እና ሙያዊ እንቅስቃሴያቸውን በሚሰሩብት ጊዜ በዚህ ደንብ ውስጥ በተቀመጡት መርሆዎች መሰረት መተግበር አለባቸው::

# ማጠቃለያ

መልዕክት ከጄኔራል ዳይሬክተር 3
መግቢያ 5

I ይሳተፉ 8

1 የስነምግባር አውታረመረብ፡ በሁሉም ደረጃዎች 10
2 ሰራተኞች የቡድኑን የስነምግባር ህግን ደንብን ማክበር 12

II መቃወም(መዋጋት) ያሉብን ነገሮች 14

3 ሙስናን እና አላስፈላጊ ተጽዕኖን መቃወም (መዋጋ 16
4 ማጭበርበርን መቃወም(መዋጋት) 18
5 የሽብርተኝነት የገንዘብ ድጋፍን መቃወም (መዋጋት) 20
6 ከገንዘብ ማጭበርበርን መቃወም(መዋጋት) 22

III ማክበር ያሉበን ነገሮች 24

7 የድርጅቱን ሚስጢር መጠበቅ ፣ የመረጃ ስርዓቶችን ደህንነት እና የግል መረጃን ጥበቃን ማክበር 26
8 ዓለም አቀፍ ማህቀቦችን እና ኤክስፓርትቁጥጥርንማክበር 28
9 የውድድር ህግን ማክበር 30
10 ሰራተኞችን ማክበር 32
11 የአልኮል መጠጥ መጠጣጥን በተመለከት የተቀመጠውን ህግ ማክበር 34


IV ማሳውቅ 36

12 ስጦታዎችን እና ግብዣዎችን ማሳወቅ 38
13 የጥቅም ግጭቶችን ማሳውቅ 40
14 የጥቅም ግጭቶችን ማሳውቅ 42
15 የንግድ አጋሮቻችንን ተሳትፎ በአግባቡ ማስተዳደር 44

የጥቆማ ስርዐት 46

ጥቆማ ስራአትትርጓሜዎች 48


# ይሳተፉ
# ሪፖርት ያድርጉ



## ኮዱን ፍላሽ

የስነምግባር ደንቡን፣ የውስጥ አሰራሮችን ወይም ህጉን የሚጥስ ባህሪን ወይም ተግባርን በሚስጥር ጥቆማ ያድርጉ።

# I ይሳተፉ







ይሳተፉ

# የሥነ ምግባር ደንባችንን ተግባራዊ ለማድረግ እና ሰራተኞቻችን እንዲረዱት እና እንዲተገብሩት ለመርዳት፣**የሚሰራ የስነምግባር መረብ( ኔትወርክ)አዘጋጅተናልye።**



**በቡድን ውስጥ የስነ ምግባር ደንብ እና የተገዥነት ፕሮግራም ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ ለበርካታ አመታት በድርጅቱ በሁሉም ደረጃ የስነ ምግባር ተወካይ እና የስነምግባር ኮሚቴዎች ተቋቁሞ እየሰራ ነው።**

**ከሰራተኞቻችን  አንዱ አስቸጋሪ ሁኔታ ካጋጠመው** ወይም ሊወስዱት በሚችሉት እርምጃዎች ወይም ውሳኔዎች ላይ ጥርጣሬ ካደረባቸው በተዘጋጅው የስነ ምግባር መረብ(ኔትወርክ) አባላት ጋር  ትክክለኛጥያቄዎችን በመጠየቅ ወይም በማጋራት እርምጃ ለመወሰን ሊከተሏቸው የሚገቡትን ሂደቶች እገዛ ከእነሱ ማግኘት ይችላሉ።

በተጨማሪም ከሥነ ምግባር ደንቡ ወይም ከዚህ ጋር ተያያዥነት ካለው ደንብ ጋር የሚቃረን ድርጊት ጥቆማ ማድረግ ከፈለግ የስነ ምግባር መረብ (ኔትወርክ) አባል ጋር ማቅረብ ወይም ጥቆማ ማድረግ ይችላል።  ።

**እያንዳንዱ  የስነ-ምግባር ተወካዮች** ወይም የስነ-ምግባር ኮሚቴ አባላትን ማንነት የሚገልጽ እና እነርሱንም ለማግኘት የሚያስችል ዘዴ በግቢው ውስጥ መቀመጥ አለበት። የ

---

## በተለያየ ቦታዎች የሚገኙ የስነ-ምግባር ኮሚቴ አባላት እና የስነ-ምግባር መኮንኖች በሚያከናውኑዋቸው ተገባራት ላይ በከፈተኛ ደረጃ ሚስጥራዊነትን የመጠበቅ ሃላፊነት እና ግዴታ አለባቸው።

ትኩረት !

**ጥቆማ መስጫ ስራአቱን ለማግኘት የQR ይጠቀሙ**

https://groupe-castel.whispli.com/ethique-conformite

ይሳተፉ

# የስነ ምግባር ተወካይ ወይም ኮሚቴ በሁሉም ደረጃ

1

## የቡድን የሥነ ምግባር ኮሚቴ

## የቅርንጫፍ የሥነ ምግባር ኮሚቴ



ካስቴል
አፍሪካ

CASTEL AFRIQUE



ካስቴል
ወይን

CASTEL
FAMILIAL & INTERNATIONAL



ሶምዲያ

somdia
Grandir ensemble

## የአካባቢ ሥነ ምግባር መረብ

# እንደ ሰራተኛ ፣ ሁላችንም **የስራ ሀላፊነታችንን በሙሉ ታማኝነት እና የድርጅቱን መልካም ስም በማያበላሽ (በማያጠፋ) መልኩ የመስራት ሃላፊነት አለብን።**

**ሁሉም ሰራተኞቻችን የስራ ደረጃቸው ሆነ የስራ ቦታቸው ምንም ይሁን ምን የስነምግባር ህጉን ማንበብ ፤ማወቅ እና በአግባቡ እየተተገበረ መሆኑንማረጋገጥ አለባቸው።**

**የስነምግባር ደንቡ የስነ-ምግባር እና ተገዢነት ፕሮግራሞችን ማጣቀሻ ሰነድ ነው።**
ከፖሊሲዎች እና አሰራሮች ጋር ተያይዞ ለሁሉም ሰራተኞች ተግባራዊ ማደርግ ግዴታ ነው፡፡

እነዚህ ሰነዶች አንድ ላይ ሆነው የሥነ ምግባር እና የተገዢነት ቅድመ አሰራር ያካትታሉ፡

እነዚህ ሰነዶች ሰራተኞች በሙያዊ እንቅስቃሴዎቻቸው ጋር በተያያዘ ሊያጋጥሟቸው ለሚችሉ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡ ያስችላቸዋል።

ራሳንም ሆነ አንድ ቡድንን ከአደጋ ወይም ከተጠያቂነት ለመከላከል ሲባል በዚህ ደንብ እና በተገዥነት ማዕቀፍ ላይ የተቀመጡትን ደንቦች የማወቅ እና የማሳውቅ ሀላፊነት አለብን፡፡




## ማሳሰብያ

እነዚህን ደንቦች ጥሶ የተገኘ ማንኛውም ሰራተኛ **የዲሲፕሊን እርምጃ የሚወሰድበት ሲሆን ፤ ቅጣት እርምጃው እንደ ጥፋቱና ጥሰቱ ክብደት ሰራተኛው የሚሰራበት ድርጅት በሚከተልው ደንብ መሰረት ከስራ ማሰናብት እና ውል እስከማቋረጥ ሊደርስ ይችላል፡፡**
ከዚህም አልፎ ጥፋት ያጠፍውን ሰራተኛ ለፍትህ ብሄር እና ለወንጀል ክስ ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

## የስነምገባር ድንቡ አብረውን ለሚሰሩ ባለድርሻ አካላት የእኛን የስን ምግባር ደረጃ መተግበር እዲያስችላው በሰፋት እነዲደርሳቸው ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

**ቡድኑ ተመሳሳይ የስነምግባር እሴቶችን እንዲከተሉ ማረጋገጥ ላይ ልዩ ትኩረት ይሰጣል።**

ይሳተፉ

# የቡድን ሰራተኞች ስነምግባር ደንብ ተገዥነት

2

## የስነምግባር ደንቡን ማወቅና እና መመሪያዎቹን ማክበር የእኛ ሃላፊነት ነው።

### ምሳሌዎች

**አደገኛ ወይም አስቸጋሪ ሁኔታ ካጋጠመዎት:**

- ማማከር
  የስነምግባር እና ተገዢነት ስርዕትን መከተል
  የስነምግባር ደንብ ማየት
  ፖሊሲዎች እና አሰራር ሂደቶችን መከተል
  ከእነሱ ውጪ አለመሆን
- አለቃን ስለጉዳዩ ማሳወቅ ወይም መመካከር



## ጥሩ ልምዶች

እራሴን ትክክለኛ ጥያቄዎችን እጠይቃለሁ

- **ይህ ሁኔታ ያልተለመደ ነው ወይስ ሕገወጥ?**
- **ይህ ሁኔታ የቡድኑን የውስጥ ፖሊሲዎች ያከብራል?**
- **ይህ ሁኔታ እኔን ሳያሳፍረኝ ለህዝብ ይፋ መሆን ይችላል?**
- **ይህ ሁኔታ የእኔን እና የቡድኑን መልካም ስም ሊያበላሽ ይችላል?**

**አደገኛ ወይም አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥሙ ብቻዎን አይጋፈጡ!**

### ማሳሰቢያ

ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ ካለ **የስነምግባር ኮሚቴ አባለትን/አባልን ማነጋገር** ወይም የደርጅቱን የአሰራር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ።።

# ለመታገል

## ቡድኑን እና ሰራተኞቹን ከህገወጥ ድርጊቶች ይጠብቁ።



## ከዱን ፍላሽ

የስነምግባር ደንቡን፣ የውስጥ አሰራሮችን ወይም ህጉን
የሚጥስ ባህሪን ወይም ተግባርን በሚስጥር ጥቆማ ያድርጉ።




# II ለመታገል





ለመታገል

# ከሰራተኞቻችን ማካከል ማንኛውም ሰው እንደ ሙስና ወይም በሽያጭ ላይ አላስፈላጊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ማንኛውም ድርጊት መፈጸም ወይም መቀበል የለበትም፡፡

## የሙስና ድርጊት

የሙስና ድርጊት አንድን ተግባር እንዲፈጽም ፤ ውሳኔ እንዲወስንወይም የተወሰነን ውሳኔ እንዲሽር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የገንዘብ መጠን፣ ማንኛውንም ንብረት ወይም ሌሎች ጥቅሞችን ፣ መቀበልን፣ መስጠትን ወይም ቃል መግባትን ያካትታል ። የሙስና ተግባር የፈጸመ፤የተባበረ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ሙስና ተግባር ላይ የተሳተፈ በሙስና ተጠያቂ ይደረጋል፡፡ የዚህ ስምምነት ተነሳሽነት በሃላፊነት ደረጃዎች ላይ ምንም ተጽእኖ የለውም.

በተጨማሪም አንድ ሰራተኛ በቡድን ውስጥ በሚከናወኑት ተግባር ወይም ውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ላማሳድረ ሲባል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማነኛውንም የገንዘብ መጠን፤ማነኛውንም ንብረት ወይም ማንኛውንም ጥቅም መቀበል የሙስና ድርጊት ነው፡፡

## የማፋጠኛ ወይም የማመቻቻ ክፍያዎች

የሙስና ዓይነት ሲሆን ኩባንያው የሚያገኛቸውን አንዳንድ አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት ወይም አፈጻጸሙን ለማፋጠን ለመንግስት ባለሥልጣን ወይም ለሌላ ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ የሚሰጠውንማንኛውንም ዓይነት ክፍያ የሚመለከት ነው።



## የአላስፋላጊ ተጽዕኖ ድርጊቶች

ከሙስና ጋር የሚመሳሰል ባህሪ አለው ነገር ግን ይሄ 3 ሰዎች ብቻ ነው የሚያመለክተው
(፩) በውሳኔው ተጠቃሚ የሆነው፤ ጥቅማ ጥቅሞችን ወይም መዋጮን የሚሰጥ
(2) ለአንድ ግለሰብ ውለታ በመዋል በእርሱ ጋር ግንገኙነት ባለው በሶስተኛ ወገን ላይ አግባብ ያልሆነ ተጽእኖ መፍጠር ፡፡
(3) ከባለስልጣን ወይም ከህዝብ አስተዳደር የተለያዩ ጥቅሞች እንዲሰጣቸው ተጽዕኖ መፍጠር

## ማንኛውም የሙስና ወይም የጉቦ ጥያቄ ማቅረብ በራሱ እንደ ሙስና ወንጀል ይቆጠራል።

ለመታገል

# 3

# ሙስናን እና ያለ አግባብ ተጽዕኖን መዋጋት(መቃወም)

ሙሰና እና ያለአግባብ ተጽዕኖን በተመለከተ ግሩፑ የሚከተለው ፖሊሲ ፍጽም (ቅንጣት ታክል) አለመታገስ ::

## ምሳሌዎች

**የሙስና ባህሪያት፡-**

- **ለእኛ የሚጠቅመንንውሳኔ ለማግኘት ስንል ለህዝብ ባለስልጣን ወይም**ለሲቪል ሰራተኛ ጉቦ መስጠት።
- **አንድ አቅራቢን ጨረታ እንዲያሸንፍ ማድረግ በምትኩ ለመዝናናት ጉዞ እንዲያዘጋጅልን መጠየቅ። በጉዞ ምትክ** ለጨረታዎች ጥሪ አካል አቅራቢ ይምረጡ ።
- **የተጀመረን የፍርድ ሂደትን እንዲተው አንድ የህግ ባለሙያን ለልጆቹ የትምህርት እድል ማመቻቸት ወይም መስጠት።**

## ጥሩ ልምዶች

- **ስራዬን ለማከናወን ማንኛውም አይነት ክፍያ አልቀበልም**
- **በሶስተኛ ወገን ባህሪ ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ ገንዘብ፣ ስጦታዎች ወይም ሌሎች ተገቢ ያልሆኑ ጥቅሞችን በጭራሽ አላቀርብም።**
- **በሶስተኛ ወገን ወይም በራሴ ባህሪ ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ገንዘብን፣ ስጦታዎችን ወይም ሌሎች ያልተገቡ ጥቅሞችን በጭራሽ አልቀበልም።**



## ማሳሰቢያ

ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ ካለ **የስነምግባር ኮሚቴ አባለትን/አባልን ማነጋገር** ወይም የደርጅቱን የአሰራር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ።

ለመታገል

# **ማጭበርበር መተማመንን** የሚያጠፋ ከመሆኑም በላይየንግድ ድርጅታችንን ቀጣይነት  አደጋ ላይ ይጥላል:: **ከስጋታችን ጋር የተጣጣመ የቁጥጥር ስርዓትን** በመጠቀም ማጭበርበርን ለመዋጋት በማንኛውም መንገድ ቁርጠኞች ነን ።



**ማጭበርበር ሆን ተብሎ ሌሎችን ለማታለል የሚደረግ ድርጊት ነው፣  ለተጠቂው ኪሳራ የሚያስከትል ሲሆን ለወንጀለኛው በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም የሚያመጣ ነው::**

**ማጭበርበር በተለያየ መንገዶች ሊፈጸም ይችላል፣ ለምሳሌ:-**

የውሸት መረጃ (የሪፖርቶችን ማጭበርበር, ሀሰተኛ የእቃ ክፍያ ሪፖርቶች ወዘተ.);

ገንዘቦችን, ንብረቶችን እና መረጃዎችን ያለአግባብ መጠቀም(መበዝበዝ) (ያለ ክፍያ, የውሸት ወይም ከመጠን በላይ ዋጋ ያላቸው ደረሰኞች, ያልተገለጸ ጥሬ ገንዘብ መጠቀም, ወዘተ. );

የኩባንያውን ንብረት ያለአግባብ መጠቀም(መበዝበዝ) ወይም መስረቅ;

የሂሳብ ደረጃዎችን ወይም የውስጥ ቁጥጥር ሂደቶችን መፈፀም (ተመሳሳይ ክፍያ በተመሳሳይ ሰው ክፍያ እና ማረጋገጫ, ወዘተ.);

በኩባንያው ላይ ጉዳት ለማድረስ አንድን ሁኔታ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ለመጠቀም የሚያስችል እቅድ ማመቻቸት (መተግበር)::

## ትኩረት

**ማጭበርበር ብዙውን ጊዜ የሚከናወነው መረጃዎችን በማሳሳት ነው ነው፣ ለምሳሌ:-**

- **የሂሳብ መስፈርቶችን በማበላሸት**
- **የውስጥ ፖሊሲዎችን ወይም ስራ ሂደቶችን መጣስ ወይም መተላለፍ ፣**
- **የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱን አለማክበር**

ለመታገል

# ማጭበርበርን መዋጋት

4

## ምሳሌዎች

አንድ የቡድን ሰራተኛ ተመሳሳይ ስም ከሌለው አንድ ድርጅት ሂሳብ ቁጥር አቀረበልኝ እንዲከፈለው ከሚፈልግ አቀራቢ ደረሰኝ እንደተቀበለ ነገረኝ። ይህ ችግር እንደማይፈጥር እና ሁለቱ ኩባንያዎች የተያያዘ እንደሆኑ ነግሮኛል። በተጨማሪም የፋይናንስ ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ይህ መደበኛ ተግባር እንደሆነ አክለው ተናግረዋል።

**ይህን ክፍያ ማረጋገጥ አለብኝ?**

**አይ**

- ይህንን ሰራተኛ ለመርዳት ፈቃደኛ አልሆንም እና የክፍያ ጥያቄውን ወደ ያልተለመደ የሂሳብ ቁጥር እንዳስገባ የጠየቀኝንም አላጸድቅም
- ለዚህ ሰራትኛ ባህሪው ከሥነ-ምግባር ደንቦቹ ጋር የሚቃረን መሆኑን አሳውቀዋለው;
- ስለ ሁኔታው የስነ-ምግባር ተወካዮች አሳውቃለሁ።

**በማንኛውም ሁኔታ ደረሰኞችን ለመክፈል የማረጋገጫ ሂደቱን አከብራለሁ.**

## ጥሩ ልምዶች

- **የመክፈያ ዘዴዎች እና ንብረቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን በደንብ አረጋግጣለሁ።**
- **ያየሂሳብ መዝገብን የሚያረጋግጡልኝን ሰነዶች በአግባቡ አስቀምጣለው።**
- **ለውስጣዊ እና ውጫዊ ቁጥጥር አካላት ሁል ጊዜ በቅንነት መልስ እሰጣለሁ።**
- **ያየሌላ ቡድን ሰራተኛን ሚና በፍፁም አልወስድም እና በተለያዩ ደረጃዎች የአሰራር ቁጥጥር መከበራቸውን አረጋግጣለሁ።**




## ማሳሰቢያ

ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ ካለ **የስነምግባር ኮሚቴ አባለትን/አባልን ማነጋገር** ወይም የደርጅቱን የአሰራር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ።

ለመታገል

# **ሰላምን እና ደህንነትን አደጋ ላይ የሚጥሉ የአመጽ ድርጊቶችን ለመከላከል** መንግስታት እና አለምአቀፍ ድርጅቶች ያላቸውን ፍላጎት እንከተላለን ።

**የሽብርተኝነትን በገንዘብ መደገፍ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለአሸባሪ ድርጅት ገንዘብ፣ ቁሳቁስ በማቅረብ ወይም ምክር እና አገልግሎት በመስጠት የገንዘብ ድጋፍ ማድረግን ያካትታል።**

## እራስህን እንዴት መጠበቅ ይቻላል?

**የንግድ አጋሮችዎን በደንብ ማወቅ** አለብዎት , በተለይም ተገቢ ጥንቃቄዎችን በማካሄድ.በደንብ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

በክልልዎ ያለው የፀጥታ ሁኔታ አስጊ ከሆነ ወይም ግጭቶች ከተከሰቱ፣ ከንግድ አጋሮቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት ላይ ትልቅ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

የአካባቢ ሁኔታ ምንም ይሁን ምን **የንግድ ሁኔታዎች አጠቃላይ ስትራቴጂውን ማክበር እና ሳይለወጡ መቀጠል አለባቸው።**



## **ኢኮኖሚያዊ እና የገንዘብ ነክ ወንጀልን በንቃት እንዋጋለን ። ሽብርተኝነት በገንዘብ የመደገፍ ወንጀልን ለመከላከል የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን።**

ለመታገል

# የሽብርተኝነት የገንዘብ ድጋፍ መዋጋት(መቃወም)

5

## ጥሩ ልምዶች

- **አደጋዎች ተለይተው ከታወቁ ይህንን ጥያቄ በማካተትተግባራዊ ጥናት ማካሄድ**
- **ችግር ያለበትን የደህንነት ሁኔታ እና የእለት ከእለት ለውጦቹን ለቡድኑ ያሳውቁ።**
- **ከደህንነት ጋር የተያያዙ የውስጥ ደንቦችን ያክብሩ።**
- **ከቢዝነስ አጋሮቻችን በአንዱ የወንጀል ድርጊት ከተጠረጠረ የስነምግባር ኮሚቴዎቹን ያሳውቁ።**

### ምሳሌዎች

አንድ የታጠቁ ቡድን በአንድ ትልቅ መንገድ ላይ መንገዶችን በመዝጋት ተሽከርካሪዎች በገንዘብ ክፍያ እንዲያልፉ ብቻ ይፈቅዳል

**ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ፧**

ከዚህ መንገድ እርቃለው እና ወዲያውኑ የአካባቢውን የስነ-ምግባር ኮሚቴ እና የዚህን ሁኔታ የደህንነት ስራ አስኪያጅ አሳውቃለው

**ከታጣቂ ቡድኖች ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ፣ በአጋጣሚም የሚደረጉ ግንኙነቶች በጥብቅ የተከለከለ ነው።**




### ማሳሰቢያ

ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ ካለ **የስነምግባር ኮሚቴ አባለትን/አባልን ማነጋገር** ወይም የደርጅቱን የአሰራር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ።

ለመታገል

# **ለገንዘብ ማጭበርበር t** እንደ መሳሪያ እንዲጠቀሙን አንፈቅድምበተጨማሪም ለዚህ አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚችል ማንኛውንም ባህሪ እንቃወማለን።


**ህገወጥ የገንዘብ አስተዳደር (Money laundering)ማለት ከሕጋዊ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች የተገኙ ገንዘቦችን ምንጩን ለመደበቅ የሚደረግ ተግባር ነው። ይህን የ"ቆሻሻ" ገንዘብ ወደ መደበኛው የሥርዓት ኢኮኖሚ ለማስገባት የሚደረግ ተግባር ነው። ዓላማውም እነዚህን ገንዘቦች ሕጋዊ መልክ ለመስጠት ያለመ ነው።:**

## ለእኛ ያለው አደጋ ምንድን ነው?

ከንግድ ግንኙነት አንፃር የተከፈለልንን የገንዘብ ምንጭ ለይተን ማወቅ ባለመቻላችን ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር አደጋ ለከሰት ይችላል ።

## ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነጥብ

ሁሉም ሰራተኞቻችን ከፍተኛ ጥንቃቄ እና የውስጥ አሰራርን በተለይም የሂሳብ አያያዝ እና የሶስተኛ ወገን አስተዳደርን በጥብቅ መከተል አለባቸው።
የገንዘብ አጠቃቀሙ የገንዘብ ምንጭን ለመለየት እንዲያስችል ፍቃድ አሰጣጥ የተገደበ መሆን አለበት.



## **የንግድ አጋሮቻችን ላይ ተገቢውን ማጣራት ማድረግ** በህገወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የመጠቀም ወንጀልን ለመከላከል ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

ለመታገል

# ከገንዘብ ማጭበርበርን(መቃወም) መዋጋት

6

## ምሳሌዎች

አንድ ደንበኛ ሁልጊዜ በዝውውር የሚከፍል ሲሆን ዛሬ ግን ገንዘብ ዝውውር ችግር ምክንያት በጥሬ ገንዘብ ለመክፈል ፈለገ ።

**ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ፧**

ምንም እንኳን የጥሬ ገንዘብ ክፍያዎች ባይከለከሉም በተለይ ደግሞ የገንዘብ ክፍያው ከፍተኛ ከሆነ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ትክክለኛነትን ማረጋገጥ ከቢዝነስ አጋሮች ጋር ተያይዘው የሚመጡትን ስጋቶች ለመተንተን ያስችላል፣ ይህም በባንክ ቆጣሪ በመክፈል ሊቀንስ ይችላል።

**ስለ ገንዘቦች አመጣጥ ጥርጣሬ ካለ, የገንዘብ ክፍያ መቀበል አይቻልም.**

## ጥሩ ልምዶች

- **አደጋዎች ተለይተው ለታወቁ ደንበኞች ተገቢውን ክትትል ወይም ትክክለኝነቱን ያካሂዱ።**
- **ልዩ መብት የተበላሹ ክፍያዎች።**
- **ለክፍያ ህጋዊ ባንኮችን መጠቀም.**
- **በአንደኛው የንግድ አጋሮቻችን ህገ-ወጥ ተግባር ከተጠረጠረ የስነ-ምግባር ኮሚቴውን ያሳውቁ።**



## ማሳሰቢያ

ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ ካለ **የስነምግባር ኮሚቴ አባለትን/አባልን ማነጋገር** ወይም የደርጅቱን የአሰራር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ።

# የስነምግባር ደንቡን ያክብሩ



የሰራተኞችንም ሆነ የቡድኑን ታማኝነት ለማረጋገጥ ምስክር ሆኑ ተጎጂ ጥቆማ ያድርጉ

## ከዱን ፍለሸ

የስነምግባር ደንቡን፣ የውስጥ አሰራሮችን ወይም ህጉን የሚጥስ ባህሪን ወይም ተግባርን በሚስጥር ጥቆማ ያድርጉ።





# III ክብር



ክብር

# ሁላችንም የግል መረጃዎችን ከመጠበቅ ጋር የተያያዙ ህጋዊ ግዴታዎችን በማክበር የመረጃ ስርዓቶቻችንን ፣ **ምስጢራዊነት እና ታማኝነት** ለማረጋገጥ ቆርጠን ተነስተናል ።

**ሁሉም የቡድን ሰራተኞች በሙያዊ ተግባራቸው ወይም ለእነርሱ የተሰጡ የመረጃዎችን በስርዓትእና በአግባቡ የመጠቀም ሃላፊነት አለባቸው.**

**መረጃው የእኛ መሆኑን ለማረጋገጥ፡-**
- ለተሰበሰቡበት ዓላማ ወይም ለሕጋዊ ዓላማዎች ጥቅም ላይ ብቻ እንዲውሉ ማድረግ
- ሚስጥራዊነቱ በእነዚሁ ሶስተኛ ወገኖች ካልተረጋገጠ በስተቀር ለሶስተኛ ወገኖች ተፈጥሮአቸው ምንም ይሁን ምን**አይገለጹም ።**
- ትክክለኛ እና የተሟሉ እና ተገቢ ባልሆነ መንገድ ያልተቀየሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ
- በተፈቀደላቸው ሰዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተደራሽ እና ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል.

**ለግል መረጃ ልዩ ትኩረት መስጠት አለበት፣** እሱም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተለይቶ ከሚታወቅ ወይም ሊታወቅ የሚችልን ግለሰብን የሚመለከት መረጃ ነው። የመረጃው ሂደት እና አጠቃቀም ከሚመለከቱ የህግ መመሪያዎች ጋር በሙሉ መስማማት አለባቸው። በኩባንያው ውስጥ የቴክኖሎጂ ደንብ ካለ፣ ሁሉም ሰራተኞች ያለውን ደንብ መከተል እና ማክበር አለባቸው

## የአደጋ ሁኔታዎች

**ከሶስተኛ ወገን ጋር ጥሩ ግንኙነት ሲኖር ሚስጥራዊውን መረጃ አሳልፎ ለሶስተኛው ወገን መስጠት፡**

በቡድኑ ውስጥ በምታደርጉት ሚና ውስጥየሌሎች ሰራተኞችንም ወይም በቡድኑ ውስጥ ያሉ የሶስተኛ ወገኖች የግላዊ መረጃን በብዛት ልታስተዳድሩ ትችላላቹ፡፡

**በኩባንያው ውስጥ ቁልፍ ቦታ ሲይዙ,** ሶስተኛ ወገኖች እርስዎን በማስመሰል ያልተፈቀዱ ድርጊቶችን እንዲፈጽሙ ሊያበረታታ ይችላል፡፡

# የኩባንያ መረጃ ስርዓትን ለመጠቀም የሚሰጡ የይለፍ ቃሎች ( PASSWORD) ግላዊ በመሆናችው ለሌላ ሶስተኛ ወገን ማጋራት፣ መሸጥ ወይም መተላለፍ የለባቸወም።

ክብር

# ፤ የመረጃ ስርዓቶችን እና **የግል መረጃን ምስጢራዊነትን** መከበር አለበት።

7

ሁላችንም የመረጃ ስርአት ደህንነት ባለድርሻዎች ነን። እያንዳንዳችን የድርጅታችንን እና የስራ መሳሪያዎቻችንን ጥበቃ እንዲያገኙ ለማስቻል የተቋቋሙትን መሥፈርቶች በጥብቅ ማክበራችን በጣም አስፈላጊ ነው።

## ምሳሌዎች

ከማላውቀው ላኪ ኢሜይል ደርሶኛል ። ኢሜይሉ ሲንኩን እንድጫን ይጠይቀኛል ።

**ማድረግ አለብኝ?**


**አይ**

ሲንኩን ከከፈትኩ በኮምፒዩተርዎ ላይ ቫይረስ ሊጭን የሚችል ስጋት አለ ይህም አጠቃላይ የመረጃ ስርዓትዎን ሊጎዳ ይችላል.

- **ለ IT(ለመረጃ ቴክኖሎጅ) ደህንነት ክፍል አስጠነቅቃለሁ**
- **ኢሜይሉን ለ IT ደህንነት ቡድኖች ሪፖርት አደርጋለሁ**

## ጥሩ ልምዶች

- **ከማላውቃቸው ላኪዎች ወይም ለእኔ አጠራጣሪ ኢሜይሎችን ስቀበል እጠነቀቃለሁ።**
- **የቡድኑን እንቅስቃሴ የሚመለከት ምንም አይነት ጥንቃቄ የሚሻው መረጃ ለሶስተኛ ወገኖች አላስተላልፍም።**
- **የእኔን የኮምፒውተር የይለፍ ቃሎችን በጭራሽ ለማንም አላጋራም እና የይለፍ ቃሎቼን በመደበኛነት እቀይራለሁ።**




## ማሳሰቢያ

ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ ካለ **የስነምግባር ኮሚቴ አባለትን/አባልን ማነጋገር** ወይም የደርጅቱን የአሰራር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ።

ክብር

# በመንግስታት እና በአለም አቀፍ ድርጅቶች **የሚጣሉትን ሁሉንም ማዕቀቦች** እናከብራለን። ።


**ዓለም አቀፍ ቅጣቶች ማንኛውንም ዓይነት የገንዘብ ሂደቶችን፣ ንግድንና ከተወሰኑ ግለሰቦች፣ አካላት እና/ወይም አካባቢዎች ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን እና/ወይም ከተወሰኑ እቃዎች፣ አገልግሎቶች ወይም ነገሮች ጋር የሚያያዝ ማዕቀፍ ወይም መሣሪያ ሲሆኑ፣ በዝርዝሩ ላይ ያሉ ስልጣናት ያስተዳድራሉ።**

---

### እነዚህን ሀላፊነቶች መወጣት የሚቻልበት መንገድ ምንድን ነው?

በዐውደ-ጽሑፉ ዙሪያ ያለውን ሀሳብና የመናከናውነውን ስራ መመርመራችን በዚህ ረገድ የተጣሉብንን እገዳዎች ለይተን ለማወቅ ያስችለናል።

የቢዝነስ አጋሮቻችንን ማወቅ ከነሱ ጋር የታቀዱት ስራዎች ወይም ግብይቶች የተፈቀዱ መሆን አለመሆናቸውን ለማውቅ ያስችላል።



## በአጠቃላይ በንግድ ግንኙነት ውስጥ በውጭ ምንዛሪ የሚደረጉ ግብይቶች በተለይ በ ዶላር እና ባዩሮ ሚደረጉ ገብይቶች ትኩረት ሊስጣቸው ይገባል።

ክብር

# ከአለም አቀፍ ማዕቀቦች እና ወደ ውጭ የሚላኩ ነገሮች ላይ የወጡ

8

## ምሳሌዎች

በሀገር ውስጥ የተመዘገበ ቅጣት ያለበት አንድ ደንበኛ ከእኛ ጋር መስራት እና ምርቶቻችንን ማስመጣት ይፈልጋል።


**ከእሱ ጋር መስራት እንችላለን?**

### አዎ ግን...

ከእሱ ጋር ከመሥራትዎ በፊት በአገሩ ላይ የተጣለው ማዕቀብ በተግባሩ ዘርፍ ላይ ተፈፃሚ መሆኑን ማረጋገጥ እና የቡድን የሥነ ምግባር ኮሚቴን ማነጋገር አስፈላጊ ነው.

## ጥሩ ልምዶች

- **የማቀርበውን ወይም የምቀበለውን ምርቶች እና ገንዘቦች ምንጭ ወይም መድረሻ አረጋግጣለሁ።**
- **በአለም አቀፍ ማዕቀብ እና የኤክስፖርት ቁጥጥሮች ላይ ራሳችንን ከንግድ አጋሮቻችን ጥሰት እንድንጠብቅ የሚያስችለንን የውል ስምምነቶችን በውሉ ውስጥ ማካተት ።**



## ማሳሰቢያ

ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ ካለ **የስነምግባር ኮሚቴ አባለትን/አባልን ማነጋገር** ወይም የደርጅቱን የአሰራር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ፡፡

ክብር

**ፃ ውድድር ለምንሰራባቸው ሀገራት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንደሚያበረክት** እና ለተጠቃሚዎቻችን እና ደንበኞቻችን ጎጂ የሆኑ ድርጊቶችን ለመዋጋት እንደሚያስችል እርግጠኞች ነን ። ለዚህም ነው **መርሆቹን ለማክበር ቆርጠን የገባነው።**

## የሸያጭ ዋጋ ማመቻቸት


የምርቶቻችን የእንደገና ሽያጭ ዋጋዎች ለደንበኞቻችን ማነቃቂያ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን በማንኛውም ሁኔታ ግን ግዳጅ አንጥልም፡፡
እንደ ገለልተኛ የኢኮኖሚ ተዋናይ ደንበኞቻችን የድጋሚ ሽያጭ ዋጋቸውን የመወሰን ነፃነት አላቸው፣ አግባብነት ያለው ህግ በሌላ መልኩ ካልቀረበ በስተቀር።

## ሕገወጥ ስምምነት

ብዙ ኩባንያዎች በውሳኔ፣ በስምምነት ወይም በሌላ በማንኛውም የተቀናጀ አሠራር ነፃ ውድድርን የማዛባት ዓላማ ወይም ውጤት ሲኖራቸው ሕገ-ወጥ ስምምነት ይሆናል።
ለምሳሌ የሚጠየቁትን ዋጋዎች ለማስተካከል ከተወዳዳሪ ጋር ስምምነት ማድረግ የተከለከለ እና ህገ ወጥ ስምምነት ይባላል፡፡።

## የበላይነትን አላግባብ መጠቀም

Empêcher un concurrent de ተፎካካሪውን ወደ ገበያው እንዳያድግ ወይም እንዳይገባ መከልከል ወይም ማድረግ የበላይነትን አላግባብ መጠቀም ሲሆን ክልክል ነው፡፡



ክብር

# የውድድር ህግን ማክበር

9

### ምሳሌዎች

አንድ ተወዳዳሪ ከንግድ ስትራቴጂ ጋር በተገናኘ መረጃ መለዋወጥ ይፈልጋል።

**ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ፧**


እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ ውድቅ መደረግ አለበት. ምስጢራዊ መረጃዎችን ለመለዋወጥ መደረጉ ብቻ የፉክክር መንፈስን የሚያዳክም ተግባር ነው፡፡

**ትኩረት!**

**በስምምነት ላይ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ እንዳይፈጠር ከተፎካካሪዎቻችን ጋር የሚደረግ ውይይት ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት.**

## ጥሩ ልምዶች

- **ሕገወጥ ስምምነት ተፈጠረ የሚል ግምት እንዳይፈጠር፣ ያለ ሕጋዊ ዓላማ ተፎካካሪዎችን ከማነጋገርና ከመገናኘት እቆጠባለሁ።**
- **ለደንበኞች የዳግም ሽያጭ ዋጋዎችን እመክራለሁ እና አላስገድዳቸውም።**
- **በአስጊ ወቅት ላይ ከስራ አካባቢ ውጭ ተፎካካሪዎቻችንን ከማገናኘት እቆጠባለሁ።**



### ማሳሰቢያ

ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ ካለ **የስነምግባር ኮሚቴ አባለትን/አባልን ማነጋገር** ወይም የደርጅቱን የአሰራር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ፡፡

ክብር

# ሰራተኞቻችን አክብሮት፣ከፍ ያለ ግምት፣ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ለስኬታማነት ነፃ እንደሆኑ የሚሰማቸውን አካባቢ ለመፍጠር መርዳት እንፈልጋለን ። ጥቃትን፣ ጉልበተኝነትን ወይም ትንኮሳን አንታገስም።

**እያንዳንዱ ሰራተኛ በስልጠናው እና በችሎታቸው ላይ በመመስረት ጤናቸውን እና ደህንነታቸውን እንዲሁም የቡድኑን  ውስጥ ሌሎች ሰራተኞችን እና ሶስተኛ ወገኖችን የመንከባከብ ሃላፊነት አለብን። በተለይም፣ የሚከተሉትን ባህሪዎች አንታገሥም እና ተገቢውንም እርምጃ እንውስዳለን።**




## ወሲባዊ ትንኮሳ

ይህም ማለት አንድ ሰውወሲባዊ ትርጉም ያላቸውን አስተያየቶች መስጠት ወይም ባህሪዎች ማሳየትእና አሳስፈላጊ ቦታ የመንካት  ተግባር ነው ፣ ይህም በወራዳነት ወይም በሚያዋርድ ባሕርያቸው ምክንያት ክብራቸውን የሚያዳክም፣ ጥላቻን ወይም አስጸያፊ ሁኔታ ይፈጥራል።

## የሞራል ትንኮሳ

ይህም በተደጋጋሚ ከሚፋጸሙ ድርጊት ጋር ይመሳሰላሉ (ለምሳሌ መደበኛ ስድብ፣ ከስራ ሰዓት ውጪ መደውል ውይም መልዕክት መላክ፣ ተገቢ ያልሆኑ አስተያየቶች፣ዛቻዎች፣ወዘተ.) ይህ ተግባር ለተጎጂው የስራ ሁኔታዎች እንዲባባስ ሊያደርግ ይችላል፡፡ይህ ደግም በመብቶቻቸውእና ክብራቸው ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፣ የአካል ወይም የአዕምሮ ጤና ለውጥ፣ ወይም ለሙያ እድገታቸው ስጋት ላይ ሊጥል ይችላል።

## አድልዎ(መድልዎ)

እንደ ሀይማኖት፣ የቆዳ ቀለም፣ ጎሳ፣ ዜግነት፣ ጂኦግራፊያዊ አመጣጥ፣ ጤና፣ አካል ጉዳተኝነት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ እርግዝና፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ ፖለቲካዊ ወይም ፍልስፍናዊ አስተያየቶች ባሉ መመዘኛዎች ምክንያት በሰው ላይ ተገቢ ያልሆነ ተጽእኖ መፍጠር ማለት ነው፡፡

**ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ የስራ አካባቢን ለማረጋገጥ ቁርጠኞች ነን።ሰራተኞቻችን በስራ ቦታችው ላይ የአካል እና የአእምሮ ጤናቸው የተጠበቀ እንዲሆን የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን።**

ክብር

# ሰራተኞችን ማክበር

10

## ምሳሌዎች

ባለፉት ሁለት ወራት ምርት ውጤት እያሽቆለቆለ መጥቷል እና የኔ አለቃ በጣም የሚቆጣ ፣የሚበሳጭ ፣አንዳንድ ጊዜ የቡድናችን አባላት ላይ ይዛተልይሳደባል። ስለ ጉዳዩ ሳነጋግረው አፈልጋለሁ ነገር ግን እኔም ላይ እንዳይዝት እና እንዳይሳደብ እፈራለው።።


**ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ፧**

አንተም ላይ የስራ ባልደረቦችክ ላይ የስራ ደራጃቹ ወይም ሁኔታቹ ምንም ይሁን ምንም ስነ ምግባር ይጎደለው ድርጊት መፈጸም ተቀባይነት የለውም።።

**በማንኛውንም ሁኔታ በቀጥታ ተጎጂ ብሆንም ወይም ከዚህ የስነምግባር ህግ ጋር የሚቃረን የባህሪ ምስክር ለሥነ-ምግባር ኮሚቴ ወይም ለሰው ሀብት ሥራ አስኪያጅ ሪፖርት አደርጋለሁ ወይም በቀጥታ በቡድኑ ሪፖርት ማቅረቢያ መንገድኑን ተጠቅሜ  ጥቆማ አደርጋለሁ።**

## ጥሩ ልምዶች

**ሁሉም ሰራተኞች፣ እንዲሁም የንግድ አጋሮች፣ወይም ከእኛ ጋር የሚሰራ ማንኛውም ሰው በአክብሮት እና በአግባቡ መስተናገድ አለበት።።**



## ማሳሰቢያ

ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ ካለ **የስነምግባር ኮሚቴ አባለትን/አባልን ማነጋገር** ወይም የደርጅቱን የአሰራር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ።።

# በሙያም ይሁን በንግድ ስራ ሀላፊነት ውስጥ ደንበኞቻችን አልኮል ሲጠጡ በሃላፊነት እንዲጠጡ እናበረታታለን።

**የተወሰኑ የቡድን ኩባንያዎች የአልኮል መጠጦችን ያመርታሉ እና ለገበያ ያቀርባሉ። ስለዚህ የእነዚህ ኩባንያዎች እያንዳንዳቸው ለደንበኞቻቸው እና ለቡድን ሰራተኞች በሀላፊነት ስለተሞላ የአልኮል አጠቃቀም ግንዛቤ መፍጠር አለባቸው።**

**ቡድኑ በማስታወቂያ ዘመቻዎቹ ውስጥ ከመጠን በላይ አልኮል መጠጣትን ፈጽሞ አያበረታታም እና የአልኮል መጠጦችን ከህጋዊ እድሜ በታች ለሆኑ ሸማቾች በጭራሽ አያስተዋውቅም፤አይሸጥም።**

የቡድን ሰራተኞች ምርታማነታቸውን፣ ውሳኔያቸውን እና ደህንነታቸውን በስራ ላይ እና/ወይም የስራ ባልደረቦቻቸው በአልኮል እንዲጠቁ መፍቀድ የለባቸውም።



## (የኩባንያው ሆነ የሌላ ተሽከርካሪ ወይም ማሽን በህግ ከሚፍቅድ የአልኮል ግደብ ላይ ሆኖ መንዳትም ሆነ ማንቀሳቀስ በማንኛውም ሁኔታ አይመከርም።)

ክብር

# በሀላፊነት የአልኮልን መጠቀም

11

ሁሉም ሰው ምንም ይሁን ምንም ከአልኮል ፍጆታ ጋር የሚወጡትን ህጎች እና ደንቦች የማክበር ሀላፊነት አለበት።

## ምሳሌዎች

መልካም አመታዊ ውጤቶችን ለማክበር ለመላው የሽያጭ ቡድን ዝግጅት ተዘጋጅቷል።

አልኮልም ተዘጋጅትዋል

አንዳንድ ሰራተኞች ከመጠን በላይ ይጠጣሉ እና ባህሪያቸው ይለወጣል, ይህም ለባልደረቦቻቸው ተገቢ ያልሆኑ አስተያየቶችን እና ምልክቶችን መስጠት ይጀምራሉ።.

**ትኩረት!**

**የአልኮል መጠጥ መጠጣት በምንም መልኩ ከሥነ ምግባር ደንቡ፣ ከውስጥ አሰራር ወይም ከህግ ተቃራኒ ድርጊትን እንድንፈጽም ሰበብ ሊሆነን(አይገባም) አይችልም።።**

## ጥሩ ልምዶች

- **በሥራ ሰዓት አልኮል መጠጣት በጥብቅ የተከለከለ ነው።**
- **በድርጅት ዝግጅቶች ወቅት ከመጠን በላይ የአልኮል መጠጦችን እንዲጠጡ አይመከርም።**
- **የአልኮል መጠጥ ከመጠን በላይ መጠጣትና መኪና መንዳት እርስ በርስ የማይጣጣም ከመሆኑም በላይ አንተንም ሆነ የሌሎች ሰዎች ደህንነት አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል።**



## ማሳሰቢያ

ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ ካለ **የስነምግባር ኮሚቴ አባለትን/አባልን ማነጋገር** ወይም የደርጅቱን የአሰራር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ።


ኮዱን ፍላሽ
ጥቆማ አድርግ
ማስተዳደር
ማሻሻል
የስነምግባር ደንቡን፣ የውስጥ አሰራሮችን ወይም ህጉን
የሚጥስ ባህሪን ወይም ተግባርን በሚስጥር ጥቆማ ያድርጉ።







# IV አስተዳደር

አስተዳድር

# ስጦታዎችን ወይም መስተንግዶዎችን የምንሰጠውም ሆነ የምንቀበለው ለንግድ እንቅስቃሴ ሂደት ብቻ ሲሆን እና ያልተገባ ተጸዕኖ ለመፍጠር እስካልሆኑ ድረስ ብቻ ነው፡፡



ከአጋሮቻችን እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖር ለማድረግ በተለይ በስጦታ እና በመጋዝ የሚከናወን ቢሆንም በአንዳንድ ሁኔታዎች ስጦታዎች በውሳኔ ወይም በሙስና ድርጊት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር እንደሆነ ተደርጎ ሊተረጎሙ እንደሚችሉ እንገነዘባለን። ስለዚህ ሁሉም ሰራተኞች በዚህ አካባቢ ያሉትን ደንቦች እና ህጎች ማወቅ እና መተግበር አለባቸው፡፡

### ስጦታ ምንድን ነው?

በስራ አካባቢ ውስጥ እና ከተለያዩ የንግድ ጻደኞች ጋር በተለያዩ የንግድ ግንኙነቶች ውስጥ የሚቀርብ ወይም የሚቀበል ማንኛውም ዓይነት ጥቅም፣ ስጦታ ወይም አገልግሎት።

### ግብዣ ምንድን ነው?

በስራ አካባቢ ውስጥ እና ከተለያዩ የንግድ ጻደኞች ጋር በሚካሄዱ የንግድ ግንኙነቶች ውስጥ የሚቀርቡ ወይም የሚቀበሉ ማንኛውም ዓይነት ማህበራዊ ዝግጅቶች፣ መዝናኛ፣ ጉዞ፣ ማረፍያዎች ወይም ምግብ አቅርቦት፡፡

### በተዘጋጀው መዝገብ ውስጥ ስጦታ ወይም ግብዣ መመዝገብ ግዴታ የሚሆነው መቼ ነው?

የተቀበሉት ወይም የሚቀርቡት ስጦታዎች እና ግብዣዎች የሚገመተው ዋጋ በሚመለከተው የውስጥ አሰራር ላይ ከተገለጸው ገደብ በላይ ከሆነ መመዝገብ አለባቸው።

**ትኩረት**

**አንዳንድ ስጦታዎች በጥብቅ የተከለከሉ ናቸው፤ ከሚያስከትሉት አደጋዎች የተነሳ መስጠትም ሆነ መቀበል የለብንም፡፡ ተግባራዊ በሆነው አሰራር ላይ በዝርዝር ተቀምጠው ይገኛሉ፡፡**

## ከህዝብ ተቋማት ውይም ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር ያሉ ግንኙንቶቹ የተለየ ትኩርት ሊሰጠው የሚገባ ርዕሰ ጉዳይ ነው።

አስተዳድር

# ስጦታዎችን እና ግብዣዎችን ማስተዳደር

12

## ምሳሌዎች

በዓመታዊ ድርድሮች ወቅት ከደንበኛ ውድ የሆነ ስጦታ እንደቀበለው ጠየቀኝ ። በምላሹ፣ በዋጋችን ላይ ልዩ የሆነ ቅናሽ እንድሰጠው ጠየቀኝ።

**ልቀበል?**

**አይ**

በድርድር ወቅት ድርድሩ ከሚካሄድበት ከሦስተኛ ወገን ስጦታዎችን ወይም ግብዣዎችን መቀበል **በጥብቅ የተከለከለ ነው.** በተጨማሪም የስጦታው ዋጋ ውድ መሆን የደንበኞችን ፍላጎት በተመለከተ ያለኝን ጥንቃቄ ሊያጠናክር ይገባል።

አቅራቢዬ ለዓመቱ መጨረሻ በዓላት የስጦታ ካርድ ሊሰጠኝ ይፈልጋል።

**ግብዣውን መቀበል እችላለሁ?**

**አይ**

የስጦታ ካርዶች ገንዘብ ከመክፈል ጋር ይመሳሰላሉ።።

## ጥሩ ልምዶች

**ጥሩ ልምዶች ትኩረት እሰጣለሁ፡-**
**የስጦታው መንነት**
**የስጦታው ዋጋ**
**የቀረበበት ወይም የተቀበለው ሁኔታ(አግባብ)**
**የላከውን ወይም የተቀበለውን ሰው ማንነት**

**ስጦታውን ወይም ግብዣውን በሚመለከተው አሰራር በተገለጹት ህጎች መሰረት እመዘግባለሁ።**

**በጥርጣሬ ውስጥ ከሆነ ስጦታን ወይም ግብዣን አለመቀበል ይመረጣል።**



## ማሳሰቢያ

ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ ካለ **የስነምግባር ኮሚቴ አባለትን/አባልን ማነጋገር** ወይም የደርጅቱን የአሰራር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ።

አስተዳደር

# የጥቅም ግጭት በራሱ ከሥነ ምግባር ደንቡ ጋር የሚቃረን ሁኔታ አይደለም። ,ይሁን እንጂ ወሳኔው ሳይገለጽ ወይም በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተጽእኖ በሚያሳድርበት ጊዜ፣ ማዕቀብ ሊታሰብበት ይችላል።



**የጥቅም ግጭት የሚፈጠረው በኩባንያው እና የግል ፤ የቤተሰብ ፤ የፖለቲካ ፍላጎቶች ፤ በሠራተኛ ላይ ጣልቃ የሚገቡየገንዘብ ወይም ሌሎች ፍላጎቶች ግጭት ሲፈጠር እና ለኩባንያው የተሻሉ ውሳኔዎችን የማድረግ ችሎታውን እናተግባሩን እንቅፋት ሲሆን ነው።**

**የሚከተሉት ሁኔታዎች በተለይ የጥቅም ግጭት ሊያስከትሉ ይችላሉ።**

ሙያዊ ውሳኔዎች በግል ፍላጎቶች፣ በቤተሰብ ግንኙነቶች ወይም በጓደኝነት ላይ ተጽዕኖ ሊያደርጉ ወይም ሊታዩ የሚችሉ በሚመስሉበት ጊዜ።

ከደንበኛ ወይም አቅራቢ ጋር ያለው ግንኙነት ተቀጣሪው ለቡድኑ ያለውን ታማኝነት ወይም የቡድኑን ጥቅም በተመለከተ ሙያዊ ውሳኔዎችን የማድረግ ችሎታ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ወይም ተጽዕኖ ሊያሳድር በሚችልበት ጊዜ።

በሙያዊ ተግባራቸው ወቅት የቡድን ንብረቶችን ወይም መረጃዎችን መጠቀም ለሠራተኛ የግል ጥቅም ሊያመጣ ወይም አንዱን ዘመዱን ለመጥቀም በሚሆንበት ጊዜ::

**በሙያዊ ተግባራቸው፣ እያንዳንዱ ሰራተኛ ውሳኔዎችን ለቡድኑ ጥቅም ማድረግ አለባቸው ከግል ጥቅማቸው ውጭ።ስለዚህ የሰራተኞች የግል ፍላጎቶች የቡድኑን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ችሎታ ላይ ጣልቃ መግባት የለባቸውም.**

## ሊኖሩበት የሚችሉ ማንኛውም የጥቅም ግጭት ሊፍጥሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን ሪፖርት ማድረግ የእያንዳዱ ስራተኛ ሃላፊነት ነው።

ትክክለኛ ወይም ሊከሰቱ የሚችሉ ተፅእኖዎችን ለመቀነስ ወይም እንዲጠፋ ለማድረግ እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

ትኩረት

**እነዚህን ሁኔታዎች እንዳሉ አውቆ ቡዱን በገለጸው መሰረት አለማሳወቅ ወይም ጥቆማ አለማድረግ የስነምግባር ደንቡን መጣስ ነው።**

አስተዳደር


# የጥቅም ግጭቶችን ማስተዳደር

13

የጥቅም ግጭት ካለብኝ የQR ኮድን በመጠቀም በቀጥታ መስመር ላይ ማስታወቅ አለብኝ። ይህ የማይቻል ከሆነ፣ በተቻለ ፍጥነት ለሥነምግባር ኮሚቴ ወይም ለመስመር ሥራ አስኪያጄ ማስታወቅ እችላለሁ።

## ጥሩ ልምዶች

- የግል ፍላጎቶችዎ በሙያዊ ውሳኔዎችዎ ላይ ተጽዕኖ እንዲያሳድሩ በጭራሽ አይፍቀዱ።
- ሁልጊዜም በኩባንያው ፍላጎቶች ውስጥ ፣ ያለአድሎ እና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ውሳኔዎችን



### ምሳሌዎች

በጨረታዬ ከቀረቡት አቅራቢዎች አንዱ ወንድሜ አጋር የሆነበት ኩባንያ ነው።

**ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ፧**

- **ወዲያውኑ ይህን የጥቅም ግጭት ለአካባቢው የሥነ ምግባር ኮሚቴ፣ ለመስመር ሥራ አስኪያጅዬ ወይም በኦንላይን በተጋጀው መድረክ ላይ አሳውቃለው።**
- **ሁኔታውን እስኪመረምሩ ድረስ ማንኛውንም ውሳኔ ከማድረግ እቆጠባለሁ።**
- **በሥነ ምግባር ኮሚቴው እና ለመስመር ሥራ አስኪያጅዬ በተወሰዱት የአመራር እርምጃዎች መሰረት ከባልደረባዬ አንዱ የአቅራቢውን ምርጫ እንዲያካሂድ እና ከሂደቱ እንዲወጣ ማድረግ አለብኝ.**

### ማሳሰቢያ

ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ ካለ **የስነምግባር ኮሚቴ አባለትን/አባልን ማነጋገር** ወይም የደርጅቱን የአሰራር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ፡፡

አስተዳድር

# በስነምግባር ህጋችን ውስጥ የገባነውን ቃልበማክበር **በበጎ አድራጎት ፣ በስፖንሰርሺፕ ወይም በደጋፊነት ተግባራት** ላይ ኢንቨስት በማድረግ **እሴቶቻችንን ለመካፈል** ርጥ ውሳኔ አድርገናል ።

**የድጋፍ እርምጃዎች ከተጠቃሚው ቀጥተኛ ማካካሻ ሳይኖር በአጠቃላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ ተግባራትን የሚፈጽም በቁሳቁስ መደገፍን ያካትታል።**

**ተገቢውን ትጋትና ጥንቃቄ ማድረግ**
የተጠቃሚውን ድርጅት ስም እና ታማኝነት ለማረጋገጥ ያስችላል። የስፖንሰርሺፕ ተግባር አካል በመሆን የተበረከቱትን ገንዘቦች መድረሻ ማረጋገጥም በዚህ አጋጣሚ አስፈላጊ ነው።



ትኩረት

**በምንም አይነት ሁኔታ የስፖንሰርሺፕ እርምጃ ወደ ሌላ አቅጣጫ ሊቀየር እና/ወይም በሙስና ወይም አለግባብ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ህገ-ወጥ ድርጊቶችን ለመደበቅ መጠቀም አይቻልም ።**

**የሚደርሱ ጉዳቶቸን ለመቀነስ ልገሳዎች ወይም በጎ አድራጎት ስራዎች ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል በተለይም የገንዘብ አስተዋፅኦ ያለበት ልገሳን ስምምነት መፈራረም ይገባል ።**

አስተዳድር

# የስፖንሰርሺፕ እርምጃዎችን

14

## ጥሩ ልምዶች

### ምሳሌዎች

ኩባንያው ፈቃድ ለማግኘት ብዙ ጊዜ የሚገናኝበት ማዘጋጃ ቤት በከንቲባው የሚተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ማህበርን የሚደግፍ ልገሳ ተጠይቅን።


**ልቀበል?**

**አይ**

በሕዝብ ተወካዮች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ማንኛውንም ጥያቄ አለመቀበል አለብኝ፣ በተለይ ፈቃድ እየጠበቅኩ ከሆነ ወይም በቅርቡ ለመጠየቅ እያሰብኩ ከሆነ።

ለራሴ ትክክለኛ ጥያቄዎችን እጠይቃለሁ-

- **ከዚህ ድርጊት ማን ይጠቀማል?**
- **ትክክለኛነትን ማረጋገጫ በአግባቡ ተከናውኗል?**
- **ከስነምግባር ደንቡ ጋር የተያያዙ ደንቦች የድጋፍ ስምምነቱ ላይ ተካተዋል ከእሱ ሚመነጩ ሀላፊነቶች ተፈርመዋል?**



### ማሳሰቢያ

ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ ካለ **የስነምግባር ኮሚቴ አባለትን/አባልን ማነጋገር** ወይም የደርጅቱን የአሰራር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ።

የንግድ አጋሮቻችን በደንባችን ውስጥ የተገለጹትን **የስነምግባር መስፈርቶቻችንን እንዲጋሩ እና** እኛን ወክለው ለሚሰሩት ስራዎች ተፈጻሚነት ያላቸውን **ህጎች እና መመሪያዎችን እንዲከተሉ (እንዲያከብሩ)** እንጠብቃለን ።

## እያንዳንዱ የንግድ አጋሮቻችን መርሆቹን ለማክበር በመፈረም ያረጋግጣሉ።

የቢዝነስ አጋሮቻችን ድርጊቶች በእኛ ላይ ተጽዕኖ አላቸው። በዚህም ምክንያት በንግድ ግንኙነታችን ዙርያ የሚወስዱት ውሳኔዎች ከዚህ ስነምግባር ደንብ ጋር እንዲስማሙ ለማድረግ ልዩ ትኩረት የምንሰጠው።



### ይህንን አደጋ ለመገደብ ትጋት አስፈላጊ ነው!

ወደ ንግድ ግንኙነት ከመግባታችን በፊት፣ ነገር ግን በዚህ ወቅት፣ ትክክለኝነትን ማረጋገጥ ከቢዝነስ አጋር ጋር አብሮ መስራት ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ለይተን ለማወቅ እና ትክክለኛውን ምርጫ ለምድርግ ወይም ለመቆጣጠር ወሳኝ ነው።

### ከአንድ የንግድ አጋር ጋር መስራት እንደሚችሉ እንዴት ያውቃሉ?

ትክክለኛነት ማረጋገጥ ከአንድ የንግድ አጋር ጋር ተያይዞ ምን ያህል አደጋ ሊያስከትል እንደሚንችል መተንተን መቻል አለበት። ትክክለኛነት ሲረጋገጥ አደጋ ከተለይ፣ በአጠቃላይ የድርጊት እቅድ በመተግበር ሊቀንስ ይችላል፣ ይህም ከዚህ የንግድ አጋር ጋር ያለን ግንኙነት ግምት ውስጥ ለማስገባት ይረዳናል።

**ለመተባበር ፍቃደኛ አለመሆን ፣ መልካም ያልሆነ ዝና፣ ግለፀኝነት አለመኖር ትኩረት ሊሰሰጣቸው የሚገባ ባህሪዎቹ ናቸው።**

አስተዳድር

# የቢዝነስ አጋሮቻችንን

## ተሳትፎ አስተዳድር

15

ከፍተኛ የስነምግባር ደረጃዎችን ለማክበር በህጋችን ቃል ገብተናል እናም የንግድ አጋሮቻችን ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ እንጠብቃለን።

## ምሳሌዎች

ትክክለኛነቱን በማረጋግጥበት ወቅት፣ ውል ለመዋዋል ያሰብኩት የሰራ አጋር ዋና ሥራ አስፈጻሚ በሙስና ወንጀል ተከሰው መቆየታቸውን አስተዋልኩ።

**ተያያዥ የንግድ አጋርን መጥቀስ እችላለሁ?**

**ትክክለኛነቱ በሚረጋገጥበት ወቅት አንድ አደጋ ተለይቶ ከታወቀ የሥነ ምግባር ኮሚቴው በሚመለከተው የውስጥ አሰራር መሰረት ማማከር ይኖርበታል።**

## ጥሩ ልምዶች

ለራሴ ትክክለኛ ጥያቄዎችን አጠይቃለሁ-

- **ይህ የንግድ አጋር የኩባንያውን እውነተኛ ፍላጎት ያሟላል?**
- **ከውል ግንኙነት በፊት ትክክለኛነት ማረጋገጫ መንገዶች በአግባቡ ተከናውኗል?**
- **ስነምግባር ደንቡን የያዘ(ያካተተ) ውል ተፈርሟል?**



## ማሳሰቢያ

ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ ካለ **የስነምግባር ኮሚቴ አባለትን/አባልን ማነጋገር** ወይም የደርጅቱን የአሰራር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ።



የጥቆማ
ስርዐት
ከዱን
ፍለሽ
የስነምግባር ደንቡን፣ የውስጥ አሰራሮችን ወይም ህጉን
የሚጥስ ባህሪን ወይም ተግባርን በሚስጥር ጥቆማ ያድርጉ።

ማንቂያ

# የጥቆማ ስርዐት

የስነምግባር ህጉን፣ የውስጥ አካሄዶችን ወይም ህግን የሚጥስ ማንኛውንም ባህሪ **በሚስጥር** እንዲያሳውቁ የሚያስችል **ስርዓት** አዘጋጅተናል ። እንዲሁም ማንኛውም ሰው የሰብአዊ መብቶችን እና መሰረታዊ ነጻነቶችን፣ አካባቢን፣ ጤናን እና ደህንነትን የሚቃረን ከባድ ጥሰት ጥቆማ እንዲያደርግ ይፈቅዳል።

## ምን ጥቆማ ማድረግ አለብዎት?

**ማንኛውም የስነምግባር ደንብ ጥሰት**

**ማንኛውም የውስጥ ሂደት ጥሰት**

**ማንኛውም የህግ ጥሰት**

### ምሳሌዎች

- ሙስና፣ አላስፈላጊ ተጽህኖ
- ማጭበርበር
- በሰብአዊ መብቶች እና መሰረታዊ ነፃነቶች ላይ ከባድ ጥሰት ፣ የሰዎች ጤና እና ደህንነት እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚፈጸሙ ጥሰቶችን ወዘተ...........

## እንዴት ጥቆማ መስጠት ይቻላል?

ሪፖርት ለማድረግ፣ ማንኛውም የቡድን ሰራተኛ ወይም ማንኛውም የውጭ ሰው በሁሉም የኩባንያው ደረጃዎች የሚከተሉትን ቻናሎች መጠቀም ይችላል።

**በተዘጋጁ የመጠቆምያ ስርዐቶች ጥቆማ መስጠት**

**የሥነ ምግባር ኮሚቴዎች ማሳወቅ**

**CSR ዋቢዎች**

## ጥርጣሬ

**ጥርጣሬ ካለብዎ ጥቆማ ከማድረግ ወይም የሥነ-ምግባር ኮሚቴዎች ከመናገር ወደኋላ አይበሉ።**

# ትርጓሜዎች

| | |
|---|---|
| **ተቀጣሪ:** | ማንኛውም የድርጅት ኦፊሰር፣ ተቀጣሪ፣ ጊዜያዊ ሰራተኛ፣ ተወካይ ስራ አስኪያጅ እና ተማሪዎቸ ለስልጠና ወይም ለመለማመድ የመጡ እንደ “ሰራተኛ” ይቆጠራል። |
| **የሥነ ምግባር ኮሚቴ :** | የኩባንያውን የሥነ ምግባር እና ተገዢነት ፖሊሲ በውስጥ ፖሊሲ መሰርት የሚያቋቁም እና የሚያስተዳድር አካል ነው:: |
| **የመንግስት ሰራተኛ :** | “ሲቪል ሰርቫንት” የሚለው ቃል ከዚህ በታች ካሉት ተቋማት ለአንዱ የሚሰራ ወኪልን ይጠቁማል፡-<br>• አስተዳደሮች (ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ ሰራዊት፣ ጉምሩክ፣ ፖሊስ፣ ፍትህ፣ የግብር አስተዳደር፣ ኤምባሲዎች፣ ቆንስላዎች፣ ወዘተ)፣<br>• የአገር ውስጥ የሕዝብ ተቋማት (ማዕከላዊ ባንክ፣ የሕዝብ ኩባንያዎች፣ የሕዝብ ሆስፒታሎች፣ ወዘተ)፣<br>• ዳኞች,<br>• የበላይ ክልላዊ አስተዳደሮች (የምዕራብ አፍሪካ ማዕከላዊ ባንክ፣ ወዘተ)፣<br>• ዓለም አቀፍ ተቋማት (የዓለም ባንክ፣ UN፣ WHO፣ ወዘተ)።<br>ማንኛውም የአካባቢ፣ ክልላዊ፣ ብሔራዊ ወይም የበላይ ተመራጭ ሥልጣን ያለው ሰው እንደ ሲቪል ሰርቫንት (ለምሳሌ ከንቲባዎች፣ ምክትሎች፣ምክር ቤት አባላት ፣ የማዘጋጃ ቤት አባላት፣ የፓርላማ አባላት፣ ወዘተ) እንደ መንግስት ሰራተኛ ተደርገው የቆጠራሉ ። |
| **ቡድን:** | "ቡድን" የሚለው አገላለጽ የ DF Holding SA እና ሁሉንም ቅርንጫፎች ያመለክታል. |
| **የንግድ አጋር** | ማንኛውም የቡድኑ ደንበኛ፣ የመጀመሪያ ደረጃ አቅራቢ ወይም መካከለኛ (አገልግሎት አቅራቢ፣ ወኪል፣ አማካሪ፣ ወዘተ) እንደ “የንግድ አጋር” ይቆጠራል። |
| **በፖለቲካ የተጋለጠ ሰው (PEP)፡-** | ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው በመንግስት ወይም በሕዝብ ተቋም ስም የፖለቲካ፣ የዳኝነት ወይም የአስተዳደር ተግባራትን ከአንድ አመት በታች ሲሰራ የነበር ግን መስራቱን ያቆመ። |
| **የሥነ ምግባር ዳኛ፡-** | የሥነ ምግባር ዳኛ ሠራተኞች በሕጉ የተደነገጉትን ግዴታዎች እንዲተረጉሙ ለመርዳት ወይም እሱን ለማክበር ያለውን አመለካከት ለመወሰን ለእያንዳንዱ የቡድን ኩባንያ የተመደቡ ሠራተኞች ናቸው። |

የሥነምግባር ደንቦችን ማርቀቅ እና ቅደም ተከተላቸውን ማስፈር- ዱዎ ኤጀንሲ



CASTEL
AFRIQUE

CASTEL
FAMILIAL & INTERNATIONAL



somdia
Grandir ensemble



ETH